## የ 30 ደቂቃው ቀጠሮው ምን ያህል ክፍያ ያስከፍላል?

**ከበጎ ፈቃደኛ ጠበቃ ጋር ለሚደረገው የ 30 ደቂቃ ቀጠሮ ምንም ክፍያ አይኖርም።**

## ቀጣይ የሆነ የህግ ድጋፍ ቢያስፈልገኝስ?

በጎ ፈቃደኛ ጠበቃው ጉዳይዎን ለመያዝ ከተስማማ እና የህግ ድጋፍ የገንዘብ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ አገልግሎቶቹ በነጻ ይሰጣሉ።

ነጻ የሆኑ ቀጣይነት ያላቸው አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ካልሆኑ እና የበጎ ፈቃደኛ ጠበቃውን መቅጠር ከፈለጉ፣ ስለ ክፍያዎቹ ከጠበቃው/ዋ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ሌላ ጠበቃ ለመቅጠር ከፈለጉ ለኦሪጎን ስቴት ባር ሎውየር ሪፈራል ሰርቪስ በሚከተለው ስልክ ቁጥር ይደውሉ፥ 1-800-452-7636። እነሱ በልዩ የህግ ጉዳይዎ ላይ ሊረዳዎ የሚችል ጠበቃ ስም ሊሰጡዎ ይችላሉ።

## የህግ ድጋፍ ጉዳዬን ሊቀበል ይችላል?

የኦሪገን የህግ ድጋፍ አገልግሎቶች (LASO) ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የህግ አገልግሎት የሚሰጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ የህግ ድርጅት ነው። የህግ አገልግሎቶች በ LASO ውስጥ ለማግኘት ምንም አይነት ክፍያ የለም፣ ነገር ግን ያሉን ግብዓቶች ውስን በመሆናቸው ሁሉንም ጉዳዮች አንቀበልም።

LASO በአረጋውያን ህጎች ዙሪያ ብቃት ያላቸው ጠበቆች ያሉት ሲሆን፣ በአረጋውያን መንከባከቢያ ቤቶች፣ በአዋቂ የማደጎ ቤቶች፣ በእገዛ የሚኖርባቸው የመኖሪያ ተቋማት፣ የመኖሪያ ቤት፣ በቤት ውስጥ እንክብካቤ ሜዲኬይድ፣ ሜዲኬር፣ በአረጋውያን ላይ የሚደርስ ጥቃት፣ እና አሳዳጊዎች በመሳሰሉት ላይ ድጋፍ ይሰጣሉ። ከእነዚህ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በአንዱ ላይ እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ ለ LASO በስልክ ቁጥር 503-224-4086 ይደውሉ።

## ወደ ቀጠሮዬ ስመጣ ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?

ካጋጠመዎት የህግ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ ማንኛውንም የጽሑፍ ሰነድ ይዘው ይምጡ። እነዚህ ሰነዶች ደብዳቤዎችን፣ ፎቶ ግራፎችን፣ ህጋዊ ሰነዶችን ወይም ኢሜይሎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።



## ቀጠሮ መያዝ የምችለው እንዴት ነው?

የ SLP የህግ ተቋም የጊዜ ሰሌዳ ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፥ ቀጠሮ ለመያዝ ለእርስዎ ወደሚያመቸው ማእከል ይደውሉ።

**YWCA/ East County**
600 NE 8th St, Room 100
Gresham, OR 97030
(503) 721.6771
*2 ኛ እና 4ኛ አርብ ከ 1 - 4 pm*

**Friendly House**
**1737 NW 26th Ave**
Portland, OR 97209
(503) 224-2640
*1 ኛ እና 3ኛ ሃሙስ ከ 9 am - ምሳ ሰዓት*

**Hollywood Senior Center**
1820 NE 40th
Portland, OR 97212
(503) 288-8303
*ዘወትር አርብ ከ 9 am - እኩለ ቀን*

**IRCO**
740 SE 106th
Portland, OR 97216
(503) 484.6371
*ዘወትር ሃሙስ ከ 1 - 4 pm*

**Neighborhood House**
7688 SW Capitol Hwy
Portland, OR 97219
(503) 244-5204
*2 ኛ እና 4ኛ ማክሰኞ ከ 9 am - እኩለ ቀን*

**Impact NW SE Portland**
4610 SE Belmont
Portland, OR 97215
(503) 721.6760
*ዘወትር አርብ ከ 10 am - 1 pm*

**Urban League Multi-Cultural Senior Center**
5325 NE MLK Blvd
Portland, OR 97211
(503) 280-2600
*2 ኛ፣ 3ኛ 4ኛ ማክሰኞ ከ 1-4 pm*